# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን)

**ETHIOPIAN DEMOCRATIC HIBREHIZB UNITY MOVEMENT (EDHUM)**

P.O. Box 73796 * Washington D.C. 2006-3796; E-mail: edhum2000@yahoo.com


*ሚያዝያ ፴ ቀን ፪ሺህ ዓ/ም*

## ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ!
## ለመሆኑ ኢትዮጵያ ምን በደለቻቸው?

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሰሜን-ምዕራብ የአገራችን ክፍል ወገኖቻችን ላይ ዝንታለም ጠንቶ የኖረውን ድንበር በጣሱ የሱዳን ወታደሮች የጥቃት እርምጃ እየተወሰደባቸው፣ ሰላማዊው ሕዝብ ከመሬቱ እየተፈናቀለና ንብረቱ እየተቃጠለ፣ አልፎም በገዛ አገራቸው መኖር ወንጀል ሆኖ ታስረው ወደ ሱዳን እንደተወሰዱና በእስር ላይ እንደሚገኙ ልዩ ልዩ የዓይን እማኞችን ዋቢ ያደረጉ ዘገባዎች አረጋግጠዋል፡፡ ኢዴኅአንም የዚኹኑ አሳዛኝ አድራጎት ትክክለኛነት አረጋግጧል፡፡ ድርጅታችን ለዚህ የባዕድ የግፍ ወረራ ለተጋለጠው ወገናችን ያለንን አጋርነት ስንገልጽ በከፍተኛ ወገናዊ የቁጭትና የመቆርቆር ስሜት ነው፡፡ ባስፈለገው መንገድ ሁሉ የዚህ ጥቃት ሰለባ ከሆነው ወገናችን ጎን እንደምንቆምም ያለንን ቁርጠኝነት ማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በወደፊት የጋራ ዕድሉም ይሁን በሉዓላዊነቱ የመወሰን መብቱን የተነፈገ በመሆኑ እነሆ ለቀጣይ ችግር፣ ወረራና ውርደት እየተዳረገ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነትና የሕዝብ ልዕላልና ቀበኛ የሆነው የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ በሥልጣን በቆየባቸው አሥራ-ሰባት ዓመታት ያለመቦዘን ያረጋገጠልን መራር ሃቅ ይኸንኑ ነው፡፡

የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ለም የእርሻ ቦታዎችን ለሱዳን መንግሥት አሳልፎ ለመስጠት መስማማቱን ቀደም ሲል በሱዳን ባለሥልጣናትና የዜና አውታሮች መነገሩና መዘገቡ ይታወሳል፡፡ የአቶ መለስ አገዛዝ ለሱዳን አሳልፎ የሰጠው አንጡራ የኢትዮጵያ መሬት አሁን ለጊዜው ችግሩ በተከሰተበት የጎንደር ክፍለ-አገር ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ከሁመራ እስከ ጋምቤላ ያሉ የኢትዮጵያ ክፍሎች ላይ ሊፈጸም እንደሚችል መገመቱ ቀላል ነው፡፡ የማንኛውም መንግሥት የመጀመሪያ ግዴታው የአገሩን ዜጎች ደኅንነት መጠበቅና ከውጭ ጥቃት መከላከል መሆኑ የታወቀ ቢሆንም የአቶ መለስ አገዛዝ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅምና አገራዊ አንድነት በተፃረረ ተግባር ላይ ሲሰማራ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም፡፡ በሥልጣን እስካለ ድረስም ያቆማል የሚል ብዥታ አይኖረንም፡፡ ቀደም ሲል ኤርትራ እንድትገነጠል ለተባበሩት መንግሥታት አማላጅ በመሆን የአፍሪቃ ዲፕሎማቶች በግልጽ እስኪያዝኑ ድረስ ያላሰለሰ ሙግትና ውትወታ ማድረጉና ከጥቂት ዓመታት በፊትም ውጤቱ ብላሽ የሆነ ጦርነት ከሸዓብያ ጋር በማድረግ በብዙ አሥር ሽዎች የሚቆጠሩ ዜጎች መስዋዕትነት የተገኘውን የጦር ሜዳ ድል በአፍ-ጢሙ በመከንበል የአቸናፊ ተቸናፊ በመሆን እርባና የሌላቸውና ሞተው የተቀበሩ የቅኝ ገዥዎችን ውል በማጣቀስ የትግራይን መሬቶች ለሸዓብያ ለመለገስ የተስማማ መሆኑ የሚረሳ አይደለም፡፡ በዚህም እንደ አንበሳ ድል ያደረገን የኢትዮጵያ ጦር ኃይል እንደ ጅብ እንዲያነክስ፣ ቀንዱን እንደተመታ ከብት አንገቱን እንዲቀልስ፣ መስዋዕትነቱ መና፣ ደሙ ደመ-ከልብ እንዲሆን መደረጉ የሚዘነጋ አይደለም፡፡

እንደሚታወቀው አገራችን ከወደ ሱዳን በኩል ጥቃት ሲደርስባት የአሁኑ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፡፡ ጎንደር ድረስ ዘልቆ ውድመት ያደረሰ የጥቃት ዘመቻዎች ተካሂደውባታል፡፡ ሆኖም የአካባቢው ሕዝብ በተለይና በአጠቃላይም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተባበረ ክንዱና በከበረ መስዋዕትነቱ ወሰኑን አስከብሮ ኖሯል፡፡ እነ አፄ ቴዎድሮስ ዘብ ቆመው፣ አፄ ዮሐንስ እንደ ንጉሠ-ነገሥት አዋጊ ብቻ ሳይሆን እራሳቸው እንደ አንድ ተራ ወታደር ተሰልፈው ተዋግተውና መስዋዕት ሆነው ያስከበሩት ድንበር፣ እነሆ በሕወሓት/ኢሕአዴግ

እብሪተኛ መሪዎች ሙሉ ፈቃድ በውጭ ባዕድ ጦር እንዲደፈር፣ ሰላማዊ ዜጎች ከመሬታቸውና ከቤት ንብረታቸው በጉልበት እንዲፈናቀሉና እንዲሰቃዩ እየተደረገ ነው።
የአካባቢው ኗሪ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን እራሱ ኢሕአዴግ በልማት ስም መሬት አከራይቷቸው የልማት ሥራ የጀመሩ ባለንብረቶች ጭምር በሱዳን የባዕድ ወታደሮች ንብረታቸው እንደተወረሰባቸውና እነሱም ለእንግልትና ለእስራት እንደተዳረጉ፣ በርካቶችም ከአንጡራ መሬታቸውና እትብታቸው ከተቀበረበት ቀያቸው "የሰፈራችሁት በሱዳን መሬት ላይ ነው" ተብለው በግፍ ታስረው ወደ ሱዳን ተወስደው በእስር ላይ እንደሚገኙ የደረሰን መረጃ ያረጋግጣል። የብዙዎች ንብረት በእሳት ጋይቷል፣ ተዘርፏል፣ በመሬታቸው ላይ የሱዳን መንግሥት የጦር ሠፈርና የፖሊስ ጣቢያዎች እያቋቋመ ይገኛል። ይኸ በብዙ መስዋዕትነት የተከበረ ድንበር ተጥሶ አሁን ለሱዳን የተቸረ ለም መሬት ከአርባ ኪሎ ሜትር ያላነሰ የኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ ዘልቆ የገባ እንደሆነ ይነገራል።
ይኸ አካባቢ በተለይም ላለፉት ሰላሣ-አራት ዓመታት ለአገር አንድነት፣ ለእኩልነትና ለመብቶች መከበር ተከታታይ አምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓቶችን የታገሉ ልዩ ልዩ ድርጅቶችን ሳይሰለች ያስተናገደና ሕዝቡም በጣም አገር-ወዳድና በሁሉም አገዛዞች ብዙ ግፍ የተፈጸመበት፣ ለዳር ድንበሩ መስዋዕት ሲሆንና ዘብ ሲቆም የኖረ ታጋይ ሕዝብ ነው።

ለዚህ ዓይን ያወጣና አሳፋሪ ውርደት የመጀመሪያው ተጠያቂ ተጋብዞ የገባውና የኢትዮጵያ መሬት በችሮታ የተሰጠው የሱዳን መንግሥት ሳይሆን የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በተለይም መሪዎቹ ናቸው። የአገርን አንድነት እንዲህ ዓይን ባወጣ መልኩ ማስደፈርና አሳልፎ መስጠት፣ ለሕዝብና ለታሪክ ከበሬታ ማጣት፣ ሕዝብን ለውጭ ብዝበዛ ማጋለጥ፣ የሕዝብን አንድነትና ትስስር ሆን ብሎ መሸርሸር፣ ለሕዝብ ደኅንነት፣ ዘለቄታዊ ሰላም፣ እድገትና ብልጽግና ደንታ ቢስ መሆን፣ ወዘተ... ሁሉ ምንጫቸው አንድና አንድ ብቻ ነው፤ በትዕቢት የተወጠረ የናጠጠ በሕዝብ ላይ ያለ ንቀት!! ሁሉም ሊመልሰው የሚገባ ጥያቄ ግን ለምን? የሚለው ይሆናል።
"ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ" ነውና ይኸ በታሪክና በሕዝብ ንቀት ላይ የተመሠረተ ተግባር ሊወገዝ ይገባዋል። በእውነቱ በኢሕአዴግ መሪዎች እንደዚህ ዓይነት በሕዝብና በአገር ላይ ተደጋጋሚ በደል ሲፈጸም በትዝብትና በቁጭት የሚመለከቱ ወገኖች "ለመሆኑ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ይኸንን ያኸል በደል እንዲፈጽሙ የሚያደርጋቸው ምን ያህል ኢትዮጵያን ቢጠሉ ነው? ወይስ ኢትዮጵያ ምን በደለቻቸው?" ብለው የሚጠይቁ ብዙዎች እንደሆኑ አንጠራጠርም።

አገዛዙ ወደ መንግሥታዊ ሥልጣን እንዲወጣ የሱዳን መንግሥት ላደረገለት ከፍተኛ እርዳታ ውለታ ለመመለስም ይሁን የሱዳንን ወደብ ለመጠቀም ከማሰብ፣ የነዳጅ ችሮታ ለማግኘትም ይሁን አገዛዙን ለሚቃሙ ክፍሎች ሱዳን በሯን እንድትዘጋ በመደለያነት የተለገሰ ስጦታ ወይም በሌላ ምክንያት፤ በሱዳን የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን በተለይም አገዛዙን ይቃወማሉ የሚባሉትን መርጦ አሳልፎ በመስጠት የተጀመረውን ይኸን በአገርና በሕዝብ ላይ የተፈጸመ ወንጀል በአገዛዙ ውስጥ ያሉትን ሁሉ ጨምሮ ኢትዮጵያዊያን በሞላ ሊያወግዙትና እስከ መጨረሻው ሊታገሉት ይገባል እንላለን።

ለዚህ የወሰን ውዝግብ አገዛዙ እንደተለመደው ከሁኔታው የማይጣጣም ምላሽ ሊሰጥ፣ አልፎም ጨርሶ ሊሸፍጥ መድፈሩ አይቀርም። "በልማት ስም ከጎረቤት አገር ጋር የተደረገ ሰላማዊ ድርድር" አድርጎም ሊያቀርበው ይችላል። ምንም ሊሸፋፈን የማይችለው ሃቅ ግን አገራዊ ድንበርን ያኸል፣ ያውም ብዙ የመስዋዕትነት ታሪክ ያለውና ትውልዶች በደምና በአጥንታቸው ያስከበሩት ድንበር፣ ሕዝብ ሳይጠየቅና ሳይመክርበት በውስጥ ድብቅ ስምምነት ተቀባይነት ያገኛል ተብሎ ሊታሰብ የማይገባው ጉዳይ መሆኑን ነው። ከሱዳን ጋር "ስምምነት" የሚባል ነገርም ካለ ሌላው ቢቀር የኢሕአዴግ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55 በሚያዘው መሠረት ያለው ፓርላማ ጉዳዩ ቀርቦለት ሊያየውና ሊያጸድቀው በተገባ ነበር።

ስለሆነም፤ ይኸንን አገራዊ ጉዳይ በተመለከተ ድርጅታችን፤

1) ይኽ ፀረ-አገርና ፀረ-ሕዝብ ድርጊት በዜጎች ላይ የሚያደርሰው ግፍ በአስቸኳይ እንዲቆምና ለደረሰውም ውርደትና ውድመት ሙሉ ኃላፊነቱን የሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ ተቀብሎ ለተፈናቀሉ ወገኖች አስፈላጊው ካሣና እርዳታ ተሰጥቷቸው ወደ ቦታቸው እንዲመለሱና መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲደረግ፣

2) ለዚኽ ወሰን መጣስና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ በደል መፈጸም የሕግ ባለሙያዎችን፣ የአገር ሽማግሌዎችን፣ የታሪክና የመልክዓ-ምድር ባለ ሙያዎችን እንዲሁም የአካባቢው ሕዝብ መርጦ የሚሰይማቸው ዜጎችን የጨመረ ተአማኒነት ያለው አጣሪ አካል በአስቸኳይ እንዲቋቋም፤

3) ይኽ በደል የተፈጸመውና እየተፈጸመ ያለው ለጊዜው በተወሰነ የአገሪቱ ክፍል ሆኖ ቢታይም ጉዳዩ በባዕድ የውጭ ወራሪ የአገር ድንበር መደፈርና በኢትዮጵያ ዜጎች ላይ የተፈጸመ የግፍ ድርጊት በመሆኑ፣ በውጭም ሆነ በውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንደ አንድ አገር ዜጋ በተደራጀ መልክ ተቃውሞውን በልዩ ልዩ መንገድ እንዲያሰማ፣ ለዚሁ ጉዳይ ቀደም ሲል የተቋቋመ አስተባባሪ አካል (ኮሚቴ) መኖሩ ስለተነገረንና እንቅስቃሴውንም በተግባር እያሳየ ስለሆነ፣ ለተሻለ የጋራ ውጤት ይረዳ ዘንድ ድርጅቶችም ሆኑ ስብስቦች፣ ቡድኖችም ሆኑ ግለ-ሰቦች በዚኽ ጉዳይ ዙሪያ ለማድረግ ያሰቡትን የተናጠል እንቅስቃሴ ከኮሚቴው ጋር በመመካከርና በማቀናበር ብቻ እንዲያደርጉ፤

4) ቤት ንብረታቸውን ለተቀሙ፣ ለወደመባቸውና ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን አስፈለጊው ሰብዓዊ እርዳታ በአስቸኳይ እንዲደርሳቸው እንዲደረግ፤

5) ይኽ አድራጎት የራሱን የኢሕአዴግን ሕገ-መንግሥት የተጻረረ በመሆኑ ፓርላማው በአስቸኳይ ተሰብስቦ ድንበራችን ለምን በውጭ ወራሪ ኃይል እንደተደፈረና በምንስ ምክንያት ዜጎች ለስቃይ እንደተዳረጉ አቶ መለስ ዜናዊ የአገዛዛቸውን አቋምና እርምጃ በይፋ ለሕዝብ እንዲያስረዱ እንዲደረግ፤ ይኽ ባይደረግ በዚኽ ሕገ-ወጥና ፀረ-አገር እርምጃ ተጠያቂው አቶ መለስና ቡድናቸው ብቻ ሳይሆኑ የአሁኑ ፓርላማ ውስጥ የሚገኙ የሕዝብ ተወካዮች ሁሉ እንደሆኑ ተረድተው ለጉዳዩ ተገቢውን ክብደት በመስጠት የሚጠበቅባቸውንና ያለባቸውን ሕገ-መንግሥታዊና ወገናዊ ኃላፊነት በአስቸኳይ እንዲወጡ፣

6) የሱዳን መንግሥት በግፍ አስሮ የወሰዳቸውን ኢትዮጵያውያን ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈታና ለደረሰባቸው ግፍና እንግልት፣ ለወደመባቸው ንብረት ተገቢውን ካሣ እንዲከፍላቸውና ወደየቦታቸው በሰላም እንዲመለሱ እንዲደረግ፤

7) የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ የአውሮጳ ኅብረት፣ የአፍሪቃ አንድነትና በአጠቃላይ የዓለም-አቀፉ ማኅበረሰብ ስለዚህ አደገኛና ሕገ-ወጥ ጉዳይ በግልጽ ተረድተው ችግሩ በሰላም እንዲፈታ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱና ተገቢውን ጫና እንዲያደርጉ፤

8) የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አባላት ሁሉ በራሱ አገር መንግሥት በኢሕአዴግ ፈቃድ ለውጭ ባዕድ ወረራ ተዳርጎ እየተሰቃየ ከሚገኘውና ግፍ እየተፈጸመበት ካለው ወገናችሁ ጎን ተሰልፋችሁ ድንበር ጥሶ ከገባ ከባዕድ ወራሪ እንድትከላከሉለት እንጂ በአገዛዙ የተሳሳተ መንገድ ተመርታችሁ በወገናችሁ ላይ ምንም ዓይነት የኃይል እርምጃ በመውሰድ በታሪክም በሕግም ከሚያስጠይቅና ከሚያፀጽት ከባድ ስህተት ውስጥ ከመግባት እንድትቆጠቡ፣

ጥሪያችንን እናቀርባለን፣ አበክረን እናሳስባለን፣ አጥብቀንም እንጠይቃለን፡፡

ዳር ድንበራችን ይከበር በአንድታችን!
የተባበረ ሕዝብ ያቸንፋል!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢዴኅአን